# ምዕራፍ አራት

## ሥነ-ውበታዊ እሴት (ዋጋ) (30 ክፍለ ጊዜ)

### መግቢያ

ስነ- ውበታዊ እሴት ማለት በክወናና በዕይታ ጥበባት የሚፈጠሩ ፈጠራዎች በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚጨምሩት ማህበራዊ ጥቅሞች፣ ግልጋሎቶች፣ ፋይዳና ተግባራትን ይወክላል። እነዚህ ጥበባት ማለትም ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣ ትያትርና የዕይታ ጥበብ ለአንድ ሃገር ህዝብ የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ በማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊንና ስነልቦናዊን በማደርጀት ትልቅ ጥቅም አላቸው። በመሆኑም ስነ-ውበትን ማድነቅ ከላይ ለተቀመጡት እሴቶች የጎላ አስተዋፅኦ እንዲኖራቸው ያደርጋል።

**ከዚህ ትምህርት የሚጠበቁ አጠቃላይ ውጤቶች፡-**

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ባህላዊ የክወናና የእይታ ጥበባትን ይረዳሉ።
- ስነ-ውበታዊ እሴቶችን ያውቃሉ።
- ሙዚቃን መለማመድ ያለውን ጠቀሜታ ይረዳሉ።
- የአገር በቀል ሙዚቃዎችንና ጫወታዎችን ያደንቃሉ።

### 4.1 ሙዚቃን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ (ዋጋ) (2 ክፍለ ጊዜ)

ሙዚቃ የሰዎችን ስሜት ከመቆጣጠር አልፎ የአዕምሮ ብቃትን ለማሳደግ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አለው። ከሰዎች ስሜት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ስላለው የሰዎችን አእምሮ በማዝናናት የሚሰማቸውን ስሜት እንዲገልፁ ከማድረግ በተጨማሪ የተማሪዎችን ስሜት በማነቃቃት ለትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ያግዛል ። በዚህም ምክንያት ሰዎች በየትም ቦታና አጋጣሚ ራሳቸውን የመግለፅ ብቃት እንዲኖራቸው ያግዛል።

ሙዚቃ አንዱና ዋነኛ የጥበብ አካል በመሆንዋ ሙዚቃ ከመጫወት የምናገኘው ጥቅም የተለያዩ ክህሎቶችን ማዳበር ይሆናል። ክህሎት የሚዳብረው የአካል ቅልጥፍናን እና የአእምሮ ብቃትን በማዋሃድ በመሆኑ ሙዚቃ መጫወት እነዚህን የአእምሮ ብቃትንና አካልን በማዋሃድ ተማሪዎች የፈጠራ ብቃታቸ እንዲያድግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል።

## የትምህርቱ ዝርዝር አላማ

- የአገር በቀል ሙዚቃዎችንና ጫወታዎችን ታደንቃላችሁ፡፡
- በትዝታ፣ በባቲ፣ በአንቺ ሆዬ፣ በአምባስል ቅኝቶች የተሰሩ ሙዚቃዎችን ሰምታችሁ ታደንቃላችሁ

### 4.1.1 ሙዚቃን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ (ዋጋ) (2 ክፍለ ጊዜ)

ሙዚቃ ስሜትን የምንገልጽበት አንዱ የጥበብ ክፍል ሲሆን አንድ ሙዚቃ በምንጫወትበት ጊዜ የውስጥ ስሜታችንን ደስታ፤ ሐዘን ወይንም ማንኛውንም አይነት ስሜት የምንገልፅበት ነው፡፡ ስሜታችንን በሙዚቃ የመግለፅ ልምምድ ትልቁ ጥቅም እራሳችንንም ሆነ የተማርነውን ትምህርት በአግባቡ መግለፅ እንድንችል እና በራስ መተማመን እንዲኖረን ያስችለናል፡፡

ሙዚቃ በዋናነት ዜማ፤ ሰልተ ምት እና ግጥም አሉት ፡፡ ማንኛውንም አይነት ትምህርት በሙዚቃ አጋዥነት ብንማር የተማርናቸውን ትምህርቶች ዘለግ ላሉ አመታት ማስታወስ እንድንችል ያግዘናል፡ ፡ ይህም ማለት የሙዚቃ ልምምድ የአእምሮ የማስታወስ ችሎታን ከፍ እንዲል ያደርጋል ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሙዚቃ የአእምሮ የማሰብ ብቃትን ስለሚያዳብር በተማሪዎች ላይ የፈጠራ ችሎታን ያሳድጋል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ግጥም የሙዚቃ አንዱ ክፍል በመሆኑ ግጥም እና ዜማን በሙዚቃ በመለማመድ ተማሪዎች አራቱን የቋንቋ ክህሎቶች ማለትም መስማት፤መናገር፤ማንበብ እና መፃፍ እነዲያዳብሩ ይረዳል፡፡

ሙዚቃ የማህበረሰቡ ማህበራዊ፤፤ባህላዊ፤ታሪካዊ፤ ሀገራዊ እና መንፈሳዊ ክንዋኔዎችን መግለጫ እንደመሆኑ መጠን፤ ተማሪዎች የአካባቢያቸውን ባህላዊ ክንዋኔዎች በመዝሙር እንዲገልፁ ያደርጋል፡፡

ሙዚቃ የአንድን ማህበረሰብ ያለፈውን ታሪክ እንደ መስታወት የሚያሳይ በመሆኑ ተማሪዎች ሙዚቃን በመለማመድ ውስጥ የማህበረሰባቸውን ያለፈውን ታሪክ ምን ይመስል እንደነበረ ይረዱበታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ተማሪዎች ሀገራዊ ይዘት ያላቸውን ሙዚቃዎች በመለማመድ ስለ ሀገራቸው ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ተማሪዎች ሙዚቃን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ የጎላ ነው። ምክንያቱም ሙዚቃ ከስሜት፣ ከአእምሮ እድገት፣ ከባህል እና ከታሪክ ያለው ትስስር ከፍተኛ በመሆኑ እያንዳንዱን የሙዚቃ ልምምድ በተግባር ማለማመድ፣ ማሰማት እና ሰምተው እንዲያደንቁ ማድረግ ተገቢ ነው።

የመልመጃ 1 መልስ

1. መ 2. መ 3. መ

### 4.1.2 ሀገር በቀል ሙዚቃዎችን ማወቅና ማድነቅ (1 ክፍለ ጊዜ)

ሀገር በቀል ሙዚቃዎች የሚባሉት ማህበረሰቡ በሚያደርገው የእለት ከእለት ግንኙነት የተፈጠሩ ሆነው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡ እና ማህበረሰቡ ለአስፈላጊ ተግባር የሚጠቀምባቸው ሙዚቃዎች ናቸው።

የሀገር በቀል ሙዚቃዎች የምንላቸው የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃዎችን ነው። የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ያካትታል። የመጀመሪያው የባህላዊ የሙዚቃ መሳሪዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ በዋናነትና በብዛት የምንጠቀምባቸው አራቱ ቅኝቶች ናቸው። በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በርካታ የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች አሉ። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል በአገልግሎታቸው ሲመደቡ ሦስቱን ብቻ እናያለን።

### 4.1.3 በትንፋሽ ድምፅ የሚፈጥሩ መሳሪያዎች (2 ክፍለ ጊዜ)፡-

ዋሽንት፡- ከኢትዮጵያ ባህላዊ መሳሪዎች ውስጥ የሚመደብ ሲሆን ከትንፋሽ መሳሪዎች ውስጥ የሚመደብ ነው። ራሱን ችሎ ዜማዎችን ለመጫዎት የሚያስችል ነው። በአብዛኛው እረኞች ሙዚቃን ለመጫወት የሚጠቀሙበት ነው። ዋሽንት የሚሰራው በዋናነት በሸምበቆ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በፕላስቲክ ትቦዎች መስራት ይቻላል።ዋሽንት አራትና ከዚያ በላይ ቀዳዳዎች ይኖሩታል ቀዳዳዎቹም የተመጣጠነ ርቀት አላቸው። አጨዋወቱም ቀዳዳዎቹን በጣቶቻችን በመድፈንና በመክፈት ይሆናል። ዋሽንት እንደ ቅኝቱ የተለያየ ቅጥነትና ውፍረት ወይም ቁመት ይኖረዋል።

እምቢልታ፡-ጥንታዊ ከሆኑ የኢትዮጵያ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱ ነው። አንድ እምቢልታ ብቻውን የተሟላ ዜማ ማውጣት ስለማይችል ሶስት እና ከዚ በላይ የሆኑ እምቢልታዎች በህብረት በመጫዎት የተለየ ህብረ ድምፅ ይፈጥራሉ።እምቢልታ ከጥትንት ጀምሮ በመንፈሳዊ ታቦትን ለማጀብ እና በጦርነት ወቅት ተዋጊዎችን ለማጀብ በማህበረሰብ ውስጥ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

### 4.1.4 በምት (ግጭት) የሚፈጥሩ መሳሪያዎች(2 ክፍለ ጊዜ)፡-

ከቆዳና ከተለያዩ ቆዳ መሰል ነገሮች ይሰራሉ። ድምፅ የሚያወጡት በመምታት (በመምቻ ዱላ) በመጠቀም ነው። ከበሮ በዋናነት መጥቀስ ይቻላል። የተለያዩ የከበሮ አይነቶች አሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ዐይነት ከበሮዎች የሚገኙ ሲሆን የሚሰሩትም ከእንጨት፣ ከቆርቆሮ፣ እንዲሁም ከሸክላ ሆኖ ከላይ እና ከታች የእንስሳት ቆዳ ይለብሳል፡፡ ከበሮ የምት የሙዚቃ መሳሪያ በመሆኑ ሙዚቃው ፍጥነቱን ጠብቆ እንዲሄድ የሚረዳ ነው፡፡ የተለያዩ ከበሮዎች በማህበረሰብ ውስጥ የተለያዩ ግልጋሎት አላቸው፡፡ እነርሱም ለመንፈሳዊ እና ለዓለማዊ ዜማዎች ልንጠቀማባቸው እንችላለን፡፡

### 4.1.5 በንዝረት (በክር) ድምፅ የሚፈጥሩ መሳሪያዎች (2 ክፍለ ጊዜ)

ክራር ፣በገና እና መሰንቆ ወ.ዘ.ተ የጠቀሳሉ፡፡ ክራር በንዝረት ድምፅ ከሚፈጥሩ የክር ባህላዊ መሳሪያዎች የሚመደብ ነው፡፡ ብቻውን ዜማ መጫወቻ ብቻ ሳይሆን ሙዚቃን ለማጃቢያም ያገለግላል፡፡

መሰንቆ፡- በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚታወቁ የሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱ እና ዋና ነው፡፡ የድምፅ ሳጥኑ አራት ማእዘን ቅርፅ ያለው ሲሆን የሚሰራው ከእንጨት ነው፡፡ከፊትና ከኂላ የፍየል ወይም የበግ ቆዳ ይለብሳል፡፡ መሰንቆ በአብዛኛው ብቻውን ዜማን ለመጫወት የሚያስችል ሲሆን በተጨማሪም ሙዚቃን ለማጀቢያነት ያገለግላል፡፡

በገና፡- በኢትዮጵያ ካሉ የሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ ልዩ እና በዋናነት ለመንፈሳዊ ግልጋሎት ብቻ የሚውል ነው፡፡ የሚያወጣው ድምፅ ወፍራም በመሆኑ የሰዎችን ስሜት ማረጋጋት አቅም አለው፡፡

በሀገራችን ሙዚቃ ውስጥ በአብዛኛው የምንጠቀማቸው የሙዚቃ ቅኝቶች በአምስት ድመፆች ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ አምስት የተለያዩ የሙዚቃ ድመፆችን የያዘ የሙዚቃ ቅኝት ወይም ስኬል (ፔንታቶኒክ) ይባላል፡፡ እነርሱም በዋናነት በኢትዮጵያ ውስጥ ምንጠቀምባቸው ትዝታ፣ባቲ፣ አምባሰል እና አንቺ ሆዬ ናቸው፡፡ በእነዚህ አራት ቅኝቶች የተሰሩ ትዝታ፣ባቲ፣ አምባሰል እና አንቺ ሆዬ የሚባሉ ዘፈኖች አሉዋቸው፡፡ ቅኝቶቹን በአግባቡ ለመረዳት በእያንዳንዱ ቅኝቶች የተሰሩትን ሙዚቃዎች በመምህራችሁ አማካኝነት ደጋግማችሁ በመስማት የእያንዳንዱ ቅኝቶች ቃና መለየትና ማድነቅ ይቻላል፡፡

ትዝታ፡- በርከት ያሉ ድምፃዊያን ትዝታ ዜማን ያዜሙ ቢሆንም በድምፃዊ መሀሙድ አህመድ የተዜመው የትዝታ ዘፈንን ደጋግሞ በማዳመጥ ትዝታ ቅኝትን መረዳት ይቻላል፡፡

ባቲ፡- በርከት ያሉ ድምፃዊያን ባቲ ዘፈንን ያዜሙ ቢሆንም በድምፃዊ ባህሩ ቃኜ የተዜመውን ዜማ ደጋግሞ ማዳመጥ ስለ ባቲ ቅኝት መረዳት ይቻላል፡፡

አምባሰል ፡- በርከት ያሉ ድምፃዊያን አምባሰል ዘፈንን ያዜሙ ቢሆንም በድምፃዊት ማሪቱ ለገሰ የተዜመው የአምባሰል ዘፈንን ደጋግሞ ማዳመጥ ስለ አምባሰል ቅኝት መረዳት ይቻላል፡፡

አንቺ ሆዬ፡- ኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛው የሰርግ ዜማዎች በአንቺ ሆዬ ቅኝት የተሰሩ በመሆናቸው የተወሰኑትን የሰርግ ሙዚቃዎችን ደጋግሞ መስማት ስለ ቅኝቱን መረዳት ያስችላል፡፡

ሙዚቃ  ድምፅን ከማድመጥ በቀጥታ የተያያዘ ነው፡፡ ሙዚቃን ማድመጥ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት ከነዚህም ጥቂቶቹ በግጥም ውስጥ ሚተላለፉትን መልዕክቶች በቀላሉ እንዲገነዘቡ ፣እንዲያደንቁ፣ እንዲተቹ ወ.ዘ.ተ… ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሙዚቃን ሲያደምጡ በሙዚቃ ውስጥ ያሉትን ግጥሞች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች ( ቀጭንና ወፍራም ድምፅ የሚያወጡትን የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዲለዩ) በተጨማሪም ኢትዮጵያ ውስጥ በዋናነት በምንጠቀማቸው ቅኝቶች የተሰሩ ሙዚቃዎችን የማድመጥ ፍላጎት እንዲያድርባቸው እና ባደመጡት ሙዚቃ መሰረት የሚሰማቸውን ስሜት በፅሁፍ እና በቃል እንዲገልፁ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

የመማር ማስተማሪያ ስልቶች

- ገላፃ ማድረግ
- የግልና የቡድን ውይይት ማካሄድ
- የግልና የቡድን ፅብረቃ ማድረግ
- የተለያዩ ቅኝቶቹን ማሰማት
- መምህር ተማሪዎች፤ መምህር ተማሪዎች መመላለስ (መለማመድ)
- የቃልና የፅሁፍ ጥያቄ
- የሙዚቃ መሳሪያዎችን በማየት፣ በመሞከር እንዲለዩ ማድረግ

የመማር ማስተማሪያ መሳሪያዎች

- የማስተማሪያ  ክፍል
- የመፃፍያ ሰሌዳ (ጥቁር ወይም ነጭ)
- የሰሌዳ መፃፍያ (ማርከር ፣ ጠመኔ)
- ኪቦርድ (ፒያኖ)
- ምስልና ድምፅ ማጫወቻ

የመልመጃ 2 መልስ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ

1. ሀ
2. ሐ
3. ሐ
4. መ
5. ለ
6. ሐ

## 4.1 የውዝዋዜ ጥበብ መለማመድ ያለው ጠቀሜታ (2 ክፍለ ጊዜ)

ክዋኔ ጥበባት ተብለው ከሚመደቡት መካከል ውዝዋዜ አንዱ ነው፡፡ ውዝዋዜ የሰውነት አካል እንቅስቃሴን በመጠቀም የሚደረግ የክዋኔ ጥበብ ነው፡፡ በዚህም ሰዎች ታሪካቸውን፡ ባህላቸውን፡ ስሜታቸውን እና ልዩ ልዩ ድርጊታቸውን በውዝዋዜ አማካኝነት ይገልጹበታል፡፡

አጥ.ጋቢ የማስተማር ውጤት

- የክዋኔ ጥበባት መለማመድ ያለው ጠቀሜታ ያውቃሉ፡፡

ዝርዝር አጥ.ጋቢ. የመማር ውጤት

- በሚና ጨዋታ፡ ውዝዋዜ ይሰራሉ፡፡
- ስለ ከኪነ ጥበባዊ ሚና ያውቃሉ፡፡

የክዋኔ ጥበባት መለማመድ ያለው ጠቀሜታ

ውዝዋዜ የሰውነት አካልን በማንቀሳቀስ፡ ቅልጥፍናን ለመጎናፀፍ እና ጤናማ የሆነ ክብደት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ሰውነታችን ቀልጣፋ ሲሆን በተዘዋዋሪ መንገድ አዕምሮን ፈጣን እና ንቁ ስለሚሆን ለሌሎች ትምህርቶች ተማሪዎች የሚኖራቸውን አቀባበል ያሳድጋል፡፡ ውዝዋዜ በተለያየ መንገድ ልንመለከተው እንችላለን፡፡ የማህበራዊ ኑሮን ልምድ ለመገንባት፣ አካልን ለማዳበርና የአዕምሮን ዕውቀት ለማዳበር ይጠቅማል፡፡

የማህበራዊ ኑሮን ልምድ ለመገንባት፡- የመንፈስ ጭንቀትን ለማስወገድ ይጠቅማል፡ ከትምህርት ክፍለ ጊዜ መጀመሪያ ላይ ልጆቹ በውዝዋዜ እንዲጫወቱ፡ እንዲዝናኑ ማድረግ፡፡ የተዘጋጀ ውዝዋዜ አይነት የብሔር ብሔረሰብ ውዝዋዜ ቢሆን አሳታፊ ልጆች አቀራራቢ ስለሚሆን የቡድን ስሜትና ህብረት ለማስገኘት ይጠቅማል፡፡ በሚጫወቱት የተለያዩ ኪነ-ጥበባዊ ጨዋታዎች እራሳቸውን ችለው እንዲጫወቱ ማድረግ ኃላፊነት መውሰድ እንዲያውቁ ይጠቅማል፡፡

አካልን ለማዳበር ይጠቅማል፡- የተለያዩ ኪነ-ጥበባዊ ዕንቅስቃሴን ከሚጠይቁ ድርጊቶች መካከል ውዝዋዜ አንዱ ነው፡፡ ውዝዋዜ አካላችንን ቀልጣፋና የተስተካከለ አቋም እንዲኖረን ያስችላል፡፡ በዚህም ጤናማ ደስተኛ እንድነሆን ያደርጋል፡፡

አዕምሮን በእውቀት ለማዳበር፡- የአገርን ባህልን ታሪክ ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ በአገራችን ኢትዮጵያ ከሰማንያ በላይ ብሔረሰብ እንዳለ ይታወቃል እነዚህም ህዝቦች ታሪካቸውን ባህላቸውን ከሚገልጹበት መንገዶች መካከል ውዝዋዜ አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ ስለብሔረሰቦች ውዝዋዜ በምናጠናበት ወቅት የእውቀት አድማሳችንም በዛው ልክ ያድጋል ይሰፋል ማለት ነው፡፡

የመማር ማስተማር መሳሪያዎች

- ሙዝየም ማስጎብኘት
- የምስል ማጫወቻ
- የምስል ማሳያ ግብዓቶች

የማስተማር ስልት

- የተለያዩ ብሔረሰብ ውዝዋዜዎችን እንዲጨፍሩ ማድረግ፡፡
- በሚጨፍሩት ጭፈራዎች የሚያገኙትን ጠቀሜታ ማስረዳት፡፡

## 4.3 የትያትር ጥበብን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ

ኪነ-ጥበብ ማህበረሰብን በሰለጠነ መንገድ ለመገንባትና የፈጠራ ክህሎት ያለው ትውልድ እንዲፈጠር የሚያደርገው አስተዋፅኦ ጉልህ ነው፡፡ ስለዚህ ኪነጥበብን መረዳት እና ማወቅ ያለው ጠቀሜታ በሶስት መንገድ ከፍለን ማየት እንችላለን፡ የማህበራዊ ኑሮን ልምድ ለመገንባት፣ አካልን ለማዳበርና የአዕምሮን ዕውቀት ለማዳበር ይጠቅማል፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ**

ይህንን ትምህርት ካጠናቀቁ በኂላ፡-

- ሥነ-ውበታዊ እሴቶችን ያደንቃሉ፡፡
- የቴአትር ጠቀሜታን ይረዳሉ፡፡
- በሚና ጨዋታ ይጫወታሉ፡፡
- ስለ አገር በቀል የቴአትርና ውዝዋዜ ጥበብ ያውቃሉ፡፡

ኪነ ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያመጣውን ጠቀሜታ በሶስት መንገድ ከፍለን ማየት

እንችላለን፡፡ በመሕበራዊ፡ አካላዊና አዕምሮአዊ በማለት ዘርዝረን እንመልከታቸው፡፡

### 4.2.1 የማህበራዊ ኑሮን ልምድ ለመገንባት(1 ክፍለ ጊዜ)

የመንፈስ ጭንቀትን ለማስወገድ ይጠቅማል፡ ከትምህርት ክፍለ ጊዜ መጀመሪያ ላይ ልጆቹ እንዲጫወቱ በመዚቃ፡ በዳንስ፡ ትያትርና ስዕል እንዲዝናኑ ማድረግ፡፡ የተዘጋጀውም የጨዋታ አይነት አሳታፊ ልጆች አቀራራቢ መሆን አለበት ይህም የቡድን ስሜትና ህብረት ለማስገኘት

ይጠቅማል። ያለ መምህሩ እርዳታ እራሳቸውን ችለው እንዲጫወቱ ማድረግ እራስን በስነ ስርዓት ለማነፅ ይጠቅማል።

ልጆች ያላቸውን ዝንባሌ ወይም የተሰጣቸውን መክሊት ለማወቅ ይጠቅማል። በሚጫወቱት የተለያዩ ኪነ-ጥበባዊ ጨዋታዎች እራሳቸውን ችለው እንዲጫወቱ ማድረግ ኃላፊነት መውሰድ እንዲያውቁ ይጠቅማል።

### 4.2.2 አካልን ለማዳበር ይጠቅማል(1 ክፍለ ጊዜ)

የተለያዩ ኪነ-ጥበባዊ ዕንቅስቃሴን የሚጠይቁ ድርጊቶች መዝናናት፡ ማሰብና ማስተዋል የሚጠይቁ ጨዋታዎች እና ቅልጥፍናንና ሰውነት እንደልብ ለማዘዝ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ፡-ውዝዋዜ፡ የሰውነት አካልን እንደ ለማንቀሳቀስ፡ ቅልጥፍናን ለመጎናፀፍ እና ጤናማ የሆነ ክብደት እንዲኖረን ያደርጋል። ማሰብና ማስተዋል የታከለባቸው የዝላይ፡ የመሮጥ፡ የመቀመጥና ቁጭ ማለትን የሚጠይቁ ጨዋታዎችም አስተዋይና ሽንቃጣ የሰውነት አቋም እንዲኖራችሁ ያደርጋል።

### 4.2.3 አዕምሮን በእውቀት ለማዳበር (2 ክፍለ ጊዜ)

የአገርን ታሪክ ማወቅ አዕምሮን በእውቀት ለማበልፀግና የአገር ፍቅር እንዲኖራችሁ

ያደርጋል። በአገራችን ኢትዮጵያ በተለያየ የሙያ ስራ መስክ ተሰማርተው ስኬታማ የሆኑ ግለሰቦች ታሪክ ማወቅ መነሳሳት እንዲኖራችሁና የስራ መስካችሁንም በልጅነት እድሜያችሁ እንድታውቁ ያድርጋችኃል። ስለ አገር እና አርአያ የሆኑ ግለሰቦች ታሪክን ማወቅ የእውቀት አድማሳችሁ እንዲሰፋ እና የህይወት ግብ እንዲኖራችሁ ያደርጋል።

ከዚህ በመቀጠል ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን እንመልከት፡-

- ይህ ጨዋታ ልጆችን ያቀራርባል፡ ፈጣሪና እራስን ለመቆጣጠር እንዲሁም ለማዝናናት ይጠቅማል።

### 4.2.4 አገር በቀል ጨዋታዎች (2 ክፍለ ጊዜ)

አስቀኝ

የመማር ማስተማር ስልት

የተጫዋቾች፡- ብዛት የክፍሉ ልጆች በሙሉ

የጨዋታው አጀማመር፡- ከአንድ ጀምሮ ለእያንዳንዱ ልጅ ቁጥር ሰጥቶ በተዘጋጀው ክብ ዙሪያ እንዲቀመጡ ወይም እንዲቆሙ ማድረግ።

ጨዋታው፡- መሳቅ ወይም መነጋገር አይፈቀድም። ሁሉም ዝም ብለው ትዕዛዝ መጠበቅ

አለባቸው። ከተሰጡጥ ቁጥሮች አንዱን ጠርቶ ቁጥሩ የተጠራው ልጅ መሃል በመግባት ልጆቹን ለማሳቅ ይሞክራል። ለማሳቅ ሲል ልዩ ልዩ እንቅቃሴዎችን ያለቃላት በማሳየት ለማሳቅ

ይሞክራል፡፡

ውጤቱ፡- የሳቀ ወይም የተናገረ ከክቡ መስመርና ከጨዋታው ይወጣል፡፡ በዚህ አኳኃን ቁጥሩን እየለዋወጠ፡ በመጥራት ጨዋታውን ቀጥሎ ትዕዛዙን በመጠበቅ ሳይስቅ ወይም ሳይናገር እስከመጨረሻ የቆየ አሸናፊ ይሆናል፡፡

ዓላማውና ጥቅሙ፡- በጨዋታው አማካኝነት ልጆቹ እንዲዝናኑና እንዲደሰቱ ያደርጋቸዋል፡፡

የጨዋታው ሕግ፡- በዚህ ጨዋታ ድምጽ ማውጣት እና መናገር እዲሁም ስድብ ነክ ድርጊቶች አይፈቀድም፡፡ እንቅስቃሴውን የምታሳዩት ድምጽ አልባ እንቅስቃሴን በማድረግ ይሆናል፡፡

-የመማር ማስተማር ስልት፡- ቀጥሎ የቀረበውን ባልና ሚስት የተሰኘ ታሪክ አንብበው በድርጊት ብቻ ሶስት በመሆን ማለትም ባል፡ ሚስት እና ተማሪው በመሆን በድምጽ አልባ ድራማ መልክ በመለማመድ በጓደኞቻቸው ፊት እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ ገጸ-ባህሪያቱን ማከፋፈል በፍላጎታቸው ላይ እንዲመሰረቱ ቅድሚያ እድል ለነሱ መስጠት፡፡ በሚለማመዱበት ጊዜ መከታተል እና ድጋፍ ማድረግ፡፡

### 4.2.5 ሞኝ ባልና ሚስት(1 ክፍለ ጊዜ)

በድሮ ጊዜ ሁለት ሞኝ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ዶሮ አረዱና ሚስትየዋ ሠርታ ሊበሉ ሲሉ ለጥርሳቸው መጎርጎሪያ የሚሆን ሳር የሌለ መሆኑን ያስታውሱና ሊያመጡ ወደ ዱር ሄዱ፡፡ ወደ ዱር ሲሄዱ መንገድ ላይ አንድ ተማሪ አገኛቸው፡፡ ተማሪውም፡-

ወዴት ትሄዳላችሁ? ሲል ጠየቃቸው፡፡

ዶሮ አርደን ሰርተን አስቀምጠን ለጥርሳችን መጎርጎሪያ ሳር ልናጭድ ነው፡

ቤታችሁ የት ነው?

ያ እዛ ማዶ እመንገዱ ዳር ያለው ነው ብለው ነግረውት ወደ ሳር አጨዳ ተጓዙ፡፡ ተሜም እቤታቸው ሄደና ዶሮ ወጣቸውን ግጥም አድርጎ በልቶ ጠፋ፡፡ ባልና ሚስት ሣራቸውን አጭደው ተሸክመው እቤት ደረሱና ቢያዩ የወጡ ድስት ባዶውን ሆኖ ዝንብ ወሮታል፡፡ በዚህ ጊዜ ዶሮ ወጣቸውን ዝንብ ነው የበላው ብለው በማመን በቤቱ ውስጥ ውር ውር የሚለውን ዝንብ መግደል ጀመሩ፡፡ ዝንቦች በእንስራው፣ በምጣዱ፣ በማሰሮ ላይ ሲያርፉ እነሱን አገኛለሁ በማለት የቤቱን ዕቃ ሁሉ ሲያነክቱ ቆዩ፡፡ በመጨረሻም አንዲት ዝንብ እሴትየዋ ግንባር ላይ አረፈች፡፡ በዚህ ጊዜ ሴትየዋ ዝንቧ ተነስታ እንዳትበር ቀስ ብላ በምልክት ባሏን ጠቆመችው፡፡ ሰውየውም በያዘው ቆመጥ አስተካክሎ ግንባሯን ሲላት ጊዜ ውሃ ሳትል አረፈች፡፡

የመማር ማስተማር ስልቶች

- ገለፃ ማድረግ
- ሰርቶ ማሳየት
- በሚና ጨዋታ እንዲለማመዱ ማድረግ

የመማር ማስተማር መሳሪያዎች

- ታሪካዊ ቦታዎች፣
- ሙዝየም፣
- ፎቶግራፎች፣
- የምስል ማጫወቻ፣
- የምስል ማሳያ ግብዓቶች

## 4.4 የዕይታ ጥበባትን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ (2 ክፍለ ጊዜ)

የዕይታ ጥበባትን መስራት እና መለማመድ አንድ ሰው በሕይወቱ ውስጥ የሚያጋጥሙትን ጥሩም ሆነ መጥፎ አጋጣሚዎችን ፈጠራ በተሞላበት እና በራሱ መንገድ እንዲጋፈጥ እና እንዲወጣ አቅምን እና ችሎታን ይሰጠዋል። የዕይታ ጥበባት በባህሪያቸው አካባቢን በጥልቀት ማስተዋልን እንዲሁም በማስተዋልን ማሰብን ይጠይቃሉ። ይህም አንድን የዕይታ ጥበብ ለመስራት በምንለማመድበት ወቅት አካባቢያችንን አንድንቃኝ ፣ ተፈጥሮን እንድናስተውል፣ እንድንመረምር እና የራሳችንን ፈጠራ እንድናዳብር እድሉን ይሰጠናል።

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ

- የዕይታ ጥበባት ዘርፎችን ያውቃሉ።
- በአካባቢያቸው እና በዙሪያቹ ያሉትን ነገሮች በአስተውሎት መመልከትና መረዳት ይችላሉ።
- በአካባቢያቸው ያስለዋሉትን ነገር በዕይታ ጥበብ መግለፅ ይችላሉ።

### 4.4.1 የዕይታ ጥበባትን መስራት (መለማመድ) ያለው ጠቀሜታ (2 ክፍለ ጊዜ)

የዕይታ ጥበባትን መለማመድ (መስራት) ያለውን ጠቀሜታ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች መመልከት እንችላለን እነሱም፦ ከስነ-ውበት አንፃር፣ ስሜትን ከመግለፅ አንፃር፣ ከአዕምሮ እድገት አንፃር እንዲሁም ከማህበራዊ ግንዛቤ አንፃር ናቸው።

**4.4.2 ከስነ-ውበት አንፃር(1 ክፍለ ጊዜ)፦** ስነ ውበት ማለት ውበት ላይ ያተኮረ የፍልስፍና ዘርፍ ነው።የዕይታጥበባትን መስራት ከስነ-ዉበት አስተሳሰብ ወይም ትርጉም ጋር ቀጥተኛ

ግንኙነት አለው:: እንድንየሥነ-ጥበብ ስራ በምንሰራበት ወቅት ለስነ-ውበት እሳቤ ሰፊ ተጋላጭነት ይኖረናል:: በአንድማህበረሰብ ውስጥ ስንኖር በዚያ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ ያለውን የስነ-ውበት ሀሳብ እና አመለካከትእንድንገነዘብ እና እንድናደንቅ ይረዳናል::

4.4.3 ስሜትን ከመግለፅ አንፃር (1 ክፍለ ጊዜ)፦ የዕይታ ጥበባትን መስራት ስለ አንድ አካባቢ፣ ማህበረሰብ ወይምሁኔታ የተሰማንን ስሜት በቀለም፣ በቅርፅ፣ በመስመር በመሳሰሉት እንድንገልፅ እድልን ይሰጠናል::ይህም ስለ አንድ ነገር የተሰማንን ስሜት ለመግለጽ ወላጆቻችን ወይም ከእኛ ውጪ ሌላ ሰው ላይጥገኛ እንዳንሆን ያደርገናል:: በተጨማሪም ሀላፊነት በተሞላበት መልኩ የራሳችንን ሀሳብ እንዲሁምስሜት ለሌሎችህ እናጋራበታለን:: ይህም የራስ መተማመን እንዲኖረን ይረዳናል::

4.4.4 ከስነ-አዕምሮ አንፃር (1 ክፍለ ጊዜ)፦ የዕይታ ጥበባትን መስራት እና መለማመድ ለአንድ ሰው የአዕምሮእድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው:: ይህም የዕይታ ጥበባትን በምንሰራበት ወቅት በሚያጋጥሙንልዩ ልዩ አጋጣሚዎች አዕምሯችን የተለያዩ ዓይነት ስሜቶችን እንዲለማመድ እና እንዲያውቅብሎም ችግር በሚያጋጥመን ወቅት ደግሞ ቀላል በሆነ እና ጥበብ በተሞላበት መንገድ እንድንፈታይጠቅመናል::

4.4.5 ከማህበረሰብ አንፃር (1 ክፍለ ጊዜ)፦ የተለያየ ልማድ ካላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ተባብሮ መስራትለማህበረሰባዊ እድገት እጅግ ጠቃሚ ነው:: ለምሳሌ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የተለያየ ጠባይ፣ባህሪ፣ የኑሮ ሁኔታ፣ የትምህርት አቀባበል ያለቸው ተማሪዎች ይገኛሉ:: ከእነዚህ ተማሪዎች ጋርበጋራ መስራት፣ የተለያዩ የትምህርት መርጃ ቁሳ ቁሶችን መዋዋስ እንዲሁም ችግሮችን መፍታትየመሳሰሉትን በምሰራበት ወቅት የዕይታ ጥበብ ትምህርት እነዚህ የተለያየ ጠባይ ካላቸው ተማሪዎችጋር በጋራ እንድንሰራ ይረዳናል:: ይህም በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉትን ብዝሃ ባህሎች እንዲሁምስርዓቶች እንድናደንቅ እና እንድናከብር ያስችለናል::

4.4.6 አገር በቀል የቤት አሰራሮችን፣ ጌጣጌጦችን ማወቅ እና ማድነቅ(1 ክፍለ ጊዜ)

ሀገር በቀል ዕውቀት ማለት የአንድ ሀገር ማህበረሰቦች ከምስረታቸው ጀምሮ በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው ውስጥ እያሻሻሉ እና እያዳበሩ የሚመጡት የራሳቸው የሆነ የአኗኗር ባህል ወይም ስልት ነው:: በሀገራችን ብዙ ብሄረሰቦች እንደመኖራቸው መጠን እነዚህ ብሄረሰቦች የራሳቸው የሆነ ባህል እና ትውፊት አላቸው:: የእነዚህን ብሄረሰቦች ሀገር በቀል ዕውቀቶችን ማወቅ ሀገርና ባህልን ከማወቅ በተጨማሪ ሀገርን ለማሳደግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: ከሀገር በቀል ዕውቀቶች መካከል የዕይታ ጥበባት ውጤቶች ተጠቃሽ ናቸው:: ከእነዚህ የዕይታ ጥበባት ውስጥ የቤት አሰራሮች፣ ጌጣጌጦች፣ የአለባበስ ስርዓቶች፣ የመገልገያ ቁሳቁሶች ተጠቃሽ ናቸው:: በዚህ ንዑስ ምዕራፍም የተለያዩ አገር በቀል የቤት አሰራሮችን፣ ጌጣጌጦችን፣ የመገልገያ ቁሳቁሶችን እናያለን እንዲሁም እናደንቃለን::

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- አገር በቀል የቤት አሰራሮችን ማድነቅ ይችላላቹ
- የሀገራችንን የተለያዩ ጌጣጌጦች ያውቃሉ እንዲሁም ያደንቃሉ

የዕይታ ጥበባትን ማድነቅ የሚወሰነው የዕይታ ጥበባት ከማህበረሰቡ ታሪክ ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር እንዲሁም ይዘታቸውን በማወቅ ነው። የዕይታ ጥበብን ባህላዊ ይዘት የተሰሩበትን ቁሶች እና ጠቀሜታ እንዲሁም ስነ ውበታዊ ሀሳብ ሳይረዱ ማድነቅ ሆነ ማወቅ አስቸጋሪ ነው።

የዕይታ ጥበብ የኋላ ታሪክ እንዲሁም የተሰራበትን ቦታ መነሻ ያሳውቃል። በመቀጠል ደግሞ የዕይታ ጥበባቱን ስነ ውበታዊ ገፅታ እንድንረዳ ያደርጋል።በሀገራችን የሚገኙ የተለያዩ የቤት አሰራሮች የዕይታ ጥበባት ውጤቶች ናቸው። እንዲሁም የተለያዩ ጌጣጌጦች የየራሳቸው ባህላዊ ትርጓሜ፣ ጠቀሜታ እንዲሁም የአደራረግ ስርዓት አላቸው። በሃገራችን ያሉት ቤቶች የሚሰሩበት መንገድ የሚገኙበትን አካባቢ የአየር ጠባይ ያማከለ ሲሆን የሚሰሩባቸው ቁሶችም በአካባቢው የሚገኙ ናቸው። እነዚህን ቤቶች የማስጌጫ እና የማሳመሪያ መንገዶች ሲኖሩ ከሚያስጌጡባቸው መካከል የተለያዩ ቀለማት ያላቸው የአፈር አይነቶች በመበጥበጥ የተለያዩ ቅርፆችን እና የመስመር ዓይነቶችን በመጠቀም ግድግዳዎቻቸውን ማስዋብ የተለመደ ነው። እነዚህ በቤቶቻቸው ግድግዳዎች ላይ ስዕሎችን ለመስራት የሚጠቀሙባቸው ቀለማት በአካባቢያቸው ከሚገኙት ቀለማት ጋር ተናባቢ ናቸው።

መልመጃ 1 መልስ

1. ባህል ውስጥ ያለውን የስነ-ውበት ሀሳብ እና አመለካከት እንድንገነዘብ እና እንድናደንቅ ይረዳናል።
2. የአዕምሮ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው።

መልመጃ 2፡- በሀገራችን ካሉ ባህላዊ የቤት አሰራሮች ውስጥ አንዱን በቀለም ሰርተው ያሳዩ። የሰሩትን ስዕል አሰራሩን ይግለፁ።

ተማሪዎች የተለያዩ ፎቶግራፎችን መጠቀም ይችላሉ።

ማጠቃለያ

ስነ-ጥበባዊ እሴቶችን ማድነቅ ከተለያዩ የክወናና የዕይታ የጥበባት ሙያዎች አንፃር

አይተናል። ሀገራዊ የሆኑ ቅኝቶችንና የሙዚቃ መሳሪዎችን ከላይ ያዩትን ሌሎችንም በተለያዩ ክልሎች የሚገኙትን የሙዚቃ መሳሪዎች በደንብ እንዲያውቁ ማበረታታት አስፈላጊ ነው።

የዕይታ ጥበባት አካባቢን በጥልቀት ማስተዋልን እንዲሁም በማስተዋል ማሰብን ይጠይቃሉ። የዕይታ ጥበባት ከስነ-ዉበት አስተሳሰብ እና ትርጉም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። የዕይታ ጥበባት ስሜትን በነፃነት ለመግለጽ ይረዳሉ። የዕይታ ጥበባትን መስራት ለአዕምሮ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው። የዕይታ ጥበባት ለማህበረሰባዊ እድገት ትልቅ ድርሻ አላቸው። የዕይታ ጥበባትን ለማድነቅ የዕይታ ጥበባቱ በማህበረሰቡ ታሪክ ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ ማወቅ ተገቢ ነው። በሀገራችን ብዙ ዓይነት የቤት አሰራር አይነቶች ይገኛሉ።በሀገራችን የሚገኙ የቤት አሰራሮች አካባቢያቸውን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ናቸው።

የማጠቃለያ ምዘና መልስ

1. ከታች ለተቀመጡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. ዜማ፣ስልተ ምት እና ግጥም
2. የፈጠራ
3. መስማት፣መናገር፣መፃፍ እና ማንበ
4. የዕይታ ጥበባት አንድ ሰው በሕይወቱ ውስጥ የሚያጋጥሙትን ጥሩም ሆነ መጥፎ አጋጣሚዎችን ፈጠራ በተሞላበት እና በራሱ መንገድ እንዲጋፈጥ እና እንዲወጣ አቅምን እና ችሎታን ይሰጠዋል፡፡
5. በአራት፦ ከስነ-ውበት አንፃር፣ ስሜትን ከመግለፅ አንፃር፣ ከአዕምሮ እድገት አንፃር እና ከማህበራዊ ግንዛቤ አንፃር
6. የተለያየ ልማድ ካላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ተባብሮ መስራት፣ በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉትን ብዝሃ ባህሎች እንዲሁም ስርዓቶች እንድናደንቅ እና እንድናከብር
7. ከአካባቢ አቀማመጥ እና ከማህበረሰቡ አኗኗር ዘይቤ አንፃር

# ምዕራፍ አምስት

## ጥመርታ ዝምድናና፣ትግበራ (21 ክፍለ ጊዜ)

### መግቢያ

አንድን ሙያ በራሱ ካሉት አውዶች በተጨማሪ ከሌሎች ትምህርት አይነቶች ጋር ያለውን ተዛማጅንት ማወቅና በተገቢው መልኩ መተግበር ጠቃሚ ነው፡፡ በመሆኑም የዕይታና የክወና ጥበባት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር አዛምዶና አጣምሮ መተግበር ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደትን ይፈጥራል፡፡ ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣ ትያትር እና ስነ-ስዕል በዚህ ረገድ ያላቸውን ጥቅም በተወሰነ መልኩ እናያለን፡፡

**አጠቃላይ አላማ፡-**

ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- ከዕፀዋትና ከእንስሳት እንቅስቃሴዎች በመቅዳት ውዝዋዜዎችን እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡
- ክ.እ.ጥ. ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን ጥመርታ ያስረዳሉ
- ቤተሰባዊ ድርጊቶችን በመዝሙርና በውዝዋዜ ያከናውናሉ፡፡
- በስዕልና በፍቶግራፍ መካከል ያሉትን ልዩነት ይለያሉ፡፡

### 5.1 ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ዝምድና(2 ክፍለ ጊዜ)

ሙዚቃን በመማር ማስተማር ሂደቱ እንደ አንድ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ከማድረጉም በላይ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት አይነት የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ሙዚቃን ከተለያዩ የትምህርት አይነቶች ጋር በቀላሉ ማዛመድ ይቻላል ለምሳሌ የሂሳብ ትምህርትን ዜማ እና ግጥምን ተጠቅመን የመማር ማስተማሩን ሂደት ማከናወን ተማሪዎች አእምሮአቸው ሳይጨነቅ እና አሰልቺ ባልሆነ መንገድ በቀላሉ የሂሳብ ስሌቶችን እንዲረዱ ማድረግ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ቋንቋን፣ሳይንስን፣ሂሳብን፣ ታሪክን እና ባህልን ለማስተማር ሙዚቃን እንደ አንድ የማስተማሪ ስልት መጠቀም ውጤታማ የመማር ማስተማር እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአንድ የትምህርት ክንውን ወደ ሚቀጥለው ክንውን ለመሸጋገር ሙዚቃን መጠቀም የተማሪዎችን ስሜት በተነቃቃ ሁኔታ ለሚቀጥለው ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## ዝርዝር አላማ

- ተማሪዎች በቡድን ይዘምራሉ
- ቤተሰባዊ ድርጊቶችን የተመለከቱ መዝሙሮችን ይዘምራሉ
- ስለ ተፈጥሮ ይዘምራሉ
- የስነ ምግባር መዝሙርን ይዘምራሉ

### 5.1.1 ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ (1 ክፍለ ጊዜ)፡፡

**መዝሙር 1፡- ተፈጥሮን መንከባከብ**

የመዝሙር 1፡- ተፈጥሮን መንከባከብ

አረንጎንዴ ተክሎችን
እንከባከባቸው፣
አበቦችን መቅጠፍ፣
ወንዞችን መበከል፣
ዛፎችን መቁረጥ
በጣም አደገኛ ነው፡፡

2. የተፈጥሮ ሀብቶችን ፣
መጠበቅ ይገባል፣
ውሀን ማባከን
ተፈጥሮ ያዛባል፣
ዛፎችን መቁረጥ
መሬት ይሸረሽራል፡፡







መልመጃ 1፡-

1. ከላይ ተቀመጠውን መዝሙር መልዕክት ባጭሩ ለመምህራቸውይግለፁ
2. መዝሙሩን በግል ተለማምደው ለክፍል ጓደኞቻችሁ ያቅርቡ
3. የመዝሙሩን መልዕክት ከጓደኞቻችው ጋር ይወያዩበት

የመዝሙር 2 ፡- የስነ ምግባር መዝሙር

እኔ ሀገሬን እወዳለሁ

እናት እና አባቴን አከብራቸዋለሁ

ለታናሽ ለታላቁም እታዘዛለሁ

ሰዎችን ለመርዳት እቸኩላለሁ

አዎ

መልካምነትን አሳያለሁ፡፡



መልመጃ 2፡-

1.ከላይ ተቀመጠውን መዝሙር መልዕክት ባጭሩ ለመምህራቸውይግለፁ

2. መዝሙሩን በግል ተለማምደው ለክፍል ጓደኞቻች ያቅርቡ

3. የመዝሙሩን መልዕክት ከጓደኞቻችሁ ጋር ይወያዩበት

መዝሙር 3፡-ትምህርት ይጣፍጣል

(የትምህርት ቤት ዝማሬ)

ትምህርት ይጣፍጣል

ከማር ከወተት፤

ከማር ከወተት

ያርማል ስህተት፡፡

ውቢቷ ሀገራችን

ለምለም እናታችን፤

ትመግበናለች እንደማር ወተት፡፡



መልመጃ 3፡-

1.ከላይ የተቀመጠውን መዝሙር መልዕክት ባጭሩ ለመምህራችሁ ግለፁ

2. መዝሙሩን በግል ተለማምዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ

3. የመዝሙሩን መልዕክት ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት

መልመጃ 4

ሆሄያቱን ከኖታው ትክክለኛ የጊዜ ቆይታ ጋር በትክክለኛው ድምፅ መዘመራቸውን ማረጋገጥ፡፡

ከላይ የተቀመጡትን የመዝሙር ግጥሞች በቃላቸው ማጥናታቸውን በቃልና በፅሑፍ ማረጋገጥ፡፡

1. ከላይ የተቀመጡትን መዝሙሮች መልዕክት ባጭሩ ለመምህራቸው ይግለፁ፡፡

2. መዝሙሩን በግል ተለማምደው ለክፍል ጓደኞቻቸውሲያቅርቡ አቀራረባቸውን ይመዝኗቸው፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- የመዝሙሩን ግጥም በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ መልዕክቱን ማብራራት
- መምህሩ ስታፍ ላይ የተፃፈውን መዝሙር ቀድሞ በኪቦርድ ወይም በሌላ መሳሪያ በአግባቡ መለማመድ ያስፈልጋል፡፡
- ለማነቃቂያ የሚሆን የድምፅ ልምምድ ከመዝሙሩ በፊት ያሰሯቸው
- መዝሙሩን ስንኝ በስንኝ ከፋፍሎ ተማሪዎች እንዲዘምሩ ማድረግ
- ሙሉውን መዝሙር አንድ ላይ እንዲዘምሩ በማድረግ ሰምቶ ማስተካከያ መስጠት
- ተማሪዎችን ለየብቻ በጓደኞቻቸው ፊት እንዲዘምሩ ማድረግ፡፡
- መዝሙሩን ከተለማመዱ በኋላ ዜማውን ከምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር በማቀናጀት እነዲለማመዱ ማድረግ፡፡

የመማር ማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎች

- የመለማመጃ ክፍሎች፣
- የሙዚቃና የቪዲዮ ማጫወቻ፤
- የአካባቢ የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ኪቦርድ ወይም ፒያኖ
- የመፃፊያ ሰሌዳ፣ማርከር (ጠመኔ) ወዘተ…

5.2 የውዝዋዜና ትያትር ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያላቸው ዝምድና የውዝዋዜ ድርጊቶች በተለያየ መንገድ ከተፈጥሮ እና ከእንስሳት ይመደባሉ፡፡ ይህም ከሳይንስ ትምህርት ጋር በእጅጉ የሚዛመድ ነው፡፡ ተማሪዎች የአጸዋትን እንቅስቃሴ ለውዝዋዜ በሚያጠኑበት ወቅት ስለ እጸዋት ስነ-ተፈጥሮ እግረመንገዳቸውን ያውቃሉ ማለት ነው፡፡ ስለ እንስሳት እንቅስቃሴ ለማጥናት በሚያደርጉት ሂደት ከውዝወዋዜው ድርጊት ባለፈ ስለ እንሰሳት ስነ-ባህሪ ያውቃሉ ማለት ነው፡፡

## የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማ፡-

ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-

- በሚና ጨዋታ ከእፀዋት ውዝዋዜን እንዲቀዱ ማድረግ፡፡
- ከእንሰሳት ውዝዋዜን እንዲከትቡ ይደረጋል፡፡
- የተለያዩ አይነት የእንቅስቃሴ ምንጮችን እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

### 5.2.1 ከዕፀዋትና ከእንሰሳት እንቅስቃሴዎችና ውዝዋዜዎችን መቅዳት (2 ክፍለ ጊዜ)

ውዝዋዜ በተለያየ የመልከአ ምድራዊ ክልል በተለያየ ባህል የሚገኙ ህዝቦች የሚያውቁት፣የሚገለገሉበትና ለተለየ አላማቸው ሲሉ በወጉ የሚከሽኑት ጥበብ ነው፡፡ ውዝዋዜ ባጭሩ ከስሜት የሚፈልቅ የሚመነጭ እንቅስቃሴ እንደመሆኑ በ አያሌ ዘመናት ከ ሚቆጠረው የህብረተሰብ እድገት ጋር እያደገ ከ የዘመናት ስልጣኔ ጋር እየሰፋና እየዳበረ የመጣና ወደፊትም የሚቀጥል ዘርፍ ነው፡፡ ውዝዋዜ በተለያየ የመልከአ ምድራዊ ክልል በተለያየ ባህል የሚገኙ ህዝቦች የሚያውቁት፣የሚገለገሉበትና ለተለየ አላማቸው ሲሉ በወጉ የሚከሽኑት ጥበብ ነው፡፡ ይህንንም እንቅስቃሴ ማህበረሰቡ በአደን፣ በሰርግ፣ በልዩ ልዩ ባህላዊና ሀይማኖታዊ በዓላት፣ በእርሻና በመሳሰሉት ጉዳዮች ሲጠቀሙበት ቆይቷዋል፡፡

ውዝዋዜ ልዩ ልዩ ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴዎችን በመቅዳት ይታወቃል፡፡ ከነዚህም እንቅስቃሴዎች መካከል ዛፍ ንፋስ በሚያወዛውዘው ጊዜ ያለውን እንቅስቃሴ በመከተብ፤ እሳት ሲነድ፣ የጦጣ፣ የድመት፣ እባብ ለመናደፍ ሲል፣ ውሻ አሳዳጊውን ሲያይ እና ሌሎችም እንቅስቃሴዎችን በመቅዳት ለዳንስ ግብዓትነት ሲጠቀሙበት እንመለከታለን፡፡ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ዳንስ ውስጣዊ ስሜትን፥ ፍቅርን፥ ንዴትን፥ ቅናትን፥ ጀግንነትን፥ ሀዘንንና የአካባቢ ውበትን በማድነቅ ከቃላትና ከቁሳቁስ ቀድሞ የነበረ በጠቅላላ አካላት አማካኝነት የሚገለፅ የእንቅስቃሴ ቋንቋ ነው፡፡

በድሮ ጊዜ አባቶቻችን ለአደን በሚወጡበት ጊዜ እንስሳትን ለማደን ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን ያደርጉ ነበር፡፡

የማስተማር ዘዴዎች

- ከዚህ ቀጥሎ በፎቶ የተቀመጡትን ቀደምት የአደን እንቅስቃሴችን በቪድዮ እንዲያዩ ማድረግ፡፡
- በቀደመው ጊዜ አባቶች በአደን ላይ የሚያሳዩትን ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ፡- በማድፈጥ ጊዜ፣ እንሰሳውን ሲያባርሩ ወዘተ.... እንቅስቃሴዎችን በአንድ ላይ ከትበው በውዝዋዜ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

የመማር ማስተማር መሳሪያዎች

- የምስል ማጫወቻ፣
- ሰፊ ክፍል
- ፎቶግራፎች

ስዕል 1 በአደን ወቅት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች





ስእል 2 በአደን ወቅት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች





ከዚህ በመቀጠል የተለያዩ ተፈጥሮአዊ እና የእንስሳት እንቅስቃሴዎችን በመከተብ በውዝዋዜ አቀናጅተው እንዲያቀርቡ ማድረግ።

- ዛፍ በንፋስ ሲወዛወዝ የሚያሳየው እንቅስቃሴ።
- እባብ ለመናደፍ የሚያደርገው እንቅስቃሴ።
- ውሻ አሳዳጊውን ሲያይ የሚያደርገው እንቅስቃሴ።
- ድመት ስትጫወት የምታሳየው እንቅስቃሴ።
- እሳት ሲነድ የሚታየው እንቅስቃሴ።
- የጠጣ የምታሳየው ልዩ ልዩ እንቅስቃሴ።

የማስተማር ስልት

- የእንሰሳቱን እንቅስቃሴዎች በቪድዮ እንዲያዩ ማድረግ።
- በአካባቢያቸው ወይም በቤታቸው የሚገኙ እንስሳትን እንቅስቃሴ ከትበው እንዲመጡ ማድረግ፡ ፡
- ተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ሰራሽ የሆኑ ድርጊቶችን እሳት እና ንፋስ የሚያወዛውዘው ዛፍ ወይም ተክሎች በቪድዮ ማሳየት።
- እነዚህን እንቅስቃሴዎች ተለማምደው እንዲያቀርቡ ማድረግ።

## 5.4 የዕይታ ጥበብን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ

ተማሪዎች ቀደም ባሉት ምዕራፎች ስለ ፎርም ቅርጽ እና ቀለም ተምረዋል እንዲሁም የዕይታ ጥበባትን መለማመድ ያለውን ጠቀሜታ ተረድተዋል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የዕይታ ጥበባትን እና የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን አጣምሮ መማር ያለውን ጠቀሜታ ያያሉ በተጨማሪም የዕይታ ጥበባትን በሚማሩበት ወቅት ያገኙትን ችሎታ እና ዕውቀት ሌሎች የትምህርት አይነቶች ላይ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ይረዳሉ።

### 5.4.1 ቅርፆችን፣ ፍርሞችንና ቀለማትን ከሒሳብ የትምህርት ዓይነትና ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ

**የምዕራፉ አጥጋቢ የመመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ:-

- የዕይታ ጥበባትን ከሌሎች ትምህቶች ጋር አቀናጅቶ መማር ያለውን ጠቀሜታ ያውቃሉ
- የዕይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ያውቃሉ
- ስዕላዊ ቅርፃች ከሒሳብ እና ሳይንስ ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያውቃሉ
- ቀለማት ከሳይንስ ጋር ያላቸውን ዝምድና ያያሉ

### 5.4.2 የዕይታ ጥበብና የሒሳብ ትምህርት ጥምርታ (1 ክፍለ ጊዜ)

በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያችን እንዲሁም በኑሯችን የምንመለከታቸው ቁሶች በሒሳብ ትምህርት ውስጥ ከምናገኛቸው የተለያዩ ጂኦሜትርያዊ ቅርፆች ጋር የሚያያዙ ናቸው:: እነዚህን ቅርፆች ጂኦሜትሪያዊ እና ተፈጥሯዊ በማለት በሁለት እንከፍላቸዋለን:: ጂኦሜትሪያዊ የምንላቸው የራሳቸው ወሰናዊ መስመር፣ ጠርዝ እንዲሁም ወለል ያላቸው ባለ ሁለት አውታረ መጠን የሆኑ የተለያዩ ቅርፆች ናቸው:: እነዚህ ቅርጾች እንደ ክብ፣ አራት ማዕዘን ፣ ሶስት ማዕዘን የመሳሰሉት ናቸው:: ከቅርፆች በተጨማሪ ቀለማትን በሂሳብ ትምህርት ውስጥ በስፋት ልናገኛቸው እንችላለን በተለይም እያንዳንዳቸው ቀለማት ያላቸውን የመታየት አቅም ለማወቅ እንዲሁም ለመገልፅ ሂሳባዊ ቀመሮችን እንጠቀማለን ይህም የተለያዩ ቀለማትን ለመለየት እና የትኛው ከየትኛው የበለጠ ይታያል የሚለውን ለማውቅ በምናደርገው ሒሳባዊ ስሌት አማካኝነት የቀለማትን ባህሪ እያወቅን ሒሳባዊ ችሎታችንንም እናሳድጋለን::

### 5.4.3 የቅርፆች ዓይነት (1 ክፍለ ጊዜ)

ቅርፆች የሚገልፁት (የሚወክሉት) የራሳቸው የሆነ ባህሪያት አሏቸው:: እነዚህ ባህሪያት የሚወሰኑት በዓይናችን ካየናቸው በኋላ በሚፈጥሩብን ስሜት ነው::

**5.4.4 ሶስት ማዕዘን (1 ክፍለ ጊዜ)፦** ሶስት ማዕዘን ባለ ሶስት ጎን ቅርፅ ሲሆን በስዕል ስራ ውስጥ ሶስት ማዕዘንጠንካራ የሆነ ቅርፅ (የጥንካሬ) መገለጫ ነው::

**5.4.5 ክብ (2 ክፍለ ጊዜ) ፦** ክብ የምንለው ከሁሉም አቅጣጫ እኩል በሆነ ነጥብ ዙሪያ የተሰመረ መስመር ነው::ክብ ቅርፅ በስዕል ቋንቋ ውስጥ የሴትን ተፈጥሯዊ  ባህሪን የሚያመለክት ቅርፅ ነው::

**5.4.5 ካሬ (1 ክፍለ ጊዜ)፦** በአራቱም ማዕዘን እኩል የሆነ ቅርፅ ሲሆን በስዕል ውስጥ ክብደትን  ለማሳየት እንጠቀምበታለን::

### 5.4.6 የዕይታ ጥበብና የሳይንስ ትምህርት ጥምርታ(2 ክፍለ ጊዜ)

ሳይንስ ምልከታን እና የተለያዩ ጥያቄዎችን መመለስ ላይ እና የተለያዩ ምርምሮችን በማድረግ ላይ መሰረት ያረገ ትምህርት ነው:: የዕይታ ጥበባት ደግሞ ሀሳብን፣ ምልከታን፣ ውበትን የመሳሰሉት ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚሰሩ ናቸው:: የሳይንስ እና ስነ-ጥበብ የመጨረሻ ግባቸው የተለያየ ቢሆንም እንኳ የሚሰሩበት እና የሚተገበሩበት መንገድ ተመሳሳይ ነው፣

የዕይታ ጥበብን ለመስራት አካባቢያችንን በምናስተውልበት ወቅት የተለያዩ ሳይንሳዊ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሳይንሳዊ ዕውቀታችንን እናሳድጋለን:: እንዲሁም የምናባዊ ፈጠራ ችሎታችንን ስለምናሳድግ በሳይንስ ላይ በዐይን የማይታዩ ነገሮችን በምንማርበት ወቅት የራሳችንን ምስል እንድፈጥር እና ይመንማረውን ጥምህርት ልዩ በሆነ መንገድ መረዳት እንችላለን:: ይህም ለትምህርቱ ያለንን ፍቅር እንድናዳብር እና ትምህርቱም ቀላል እና አዝናኝ እንዲሆን ይረዳናል::

ቀለማት የሥነ ጥበብ መሰረታውያን ሲሆኑ ከሳይንስ አንፃር ስንመለከታቸው ደግሞ የራሳቸው ልኬት ያላቸው ናቸው:: እንዲሁም እርስበርስ ሲቀላቀሉ አዲስ አይነት ቀለምን ይሰጡናል:: ይህም በሳይንስ ትምህርት ውስጥ ውህድ ተብሎ ይጠራል:: ስለዚህ ቀለማትን በመጠቀም የተለያዩ ሳይንሳዊ ሙከራዎችን ማድረግ እንችላለን:: ሌላው ከቀለም ጋር የሚያያዘው ሳይንሳዊ ሙከራ የሊትመስ ወረቀትን በመጠቀም አሲድ እና ቤዝን በወረቀቱ ቀለም መለወጥ ልንለያቸው እንችላለን::

ቀለማት የስነ ጥበብ መሰረታውያን ሲሆኑ ከሳይንስ አንፃር ስንመለከታቸው ደግሞ የራሳቸው ልኬት ያላቸው ናቸው:: እንዲሁም እርስበርስ ሲቀላቀሉ አዲስ አይነት ቀለምን ይሰጡናል:: ይህም በሳይንስ ትምህርት ውስጥ ውህድ ተብሎ ይጠራል:: ስለዚህ ቀለማትን በመጠቀም የተለያዩ ሳይንሳዊ ሙከራዎችን ማድረግ እንችላለን:: ሌላው ከቀለም ጋር የሚያያዘው ሳይንሳዊ ሙከራ የሊትመስ ወረቀትን በመጠቀም አሲድ እና ቤዝን በወረቀቱ ቀለም መለወጥ ልንለያቸው እንችላለን::

5.4.7 የቀለማት መዋሀድ





የመማር ማስተማር ስልቶች

- ገለፃ ማድረግ
- ሰርቶ ማሳየት
- የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ላይ የዕይታ ጥበብን እንዲለማመዱ ማድረግ

የመማር ማስተማሪያ መሳሪያዎች

- ቀለም
- እርሳስ
- ሊትመስ ወረቀት
- አሲድ እና ቤዝ

## ማጠቃለያ

ሌሎች እውቀቶችን በሙዚቃ ማስተላለፍና እንዳይረሳ ለማድረግ የተሻለ መንገድ መሆኑን ከላይ ባየናቸው ምሳሌ መዝሙሮች አይታችኋል፡፡ ሌሎችንም ትምህርቶች በሙዚቃ በማቅረብ ጥሩ ውጤት ማስመዝግብ ይቻላል፡፡

በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያችን እንዲሁም በኑሯችን የምንመለከታቸው ቁሶች በሒሳብ ትምህርት ውስጥ ከምናገኛቸው የተለያዩ ጂኦሜትርያዊ ቅርፆች ጋር የሚያያዙ ናቸው፡፡ ቀለማትን በሂሳብ እና በሳይንስ ትምህርት ውስጥ በስፋት ልናገኛቸው እንችላለን፡፡ ቀለማት ያላቸውን የመታየት አቅም ለማወቅ እንዲሁም ለመገልፅ ሂሳባዊ ቀመሮችን እንጠቀማን፡፡ ቅርፆች የሚገልፁት (የሚወክሉት) የራሳቸው የሆነ ባህሪያት አሏቸው፡፡ የሳይንስ እና ስነ-ጥበብ የመጨረሻ ግባቸው የተለያየ ቢሆንም እንኳ የሚሰሩበት እና የሚተገበሩበት መንገድ ተመሳሳይ ነው፡፡ የዕይታ ጥበባት ለሳይንስ ትምህርት ያለንን ፍቅር እንድናዳብር እና ትምህርቱም ቀላል እና አዝናኝ እንዲሆን ይረዳናል፡፡ ቀለማት የስነ ጥበብ መሰረታውያን ሲሆኑ ከሳይንስ አንፃር ስንመለከታቸው ደግሞ ልኬት ያላቸው ናቸው፡፡

የማጠቃለያ ምዘና እና መልስ

፩ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዶ ቦታውን በትክክለኛው አረፍተ ነገር ሙሉ፡፡

1. አረንጓዴ ተክሎችን …………….
2. አበቦች …………….፣ወንዞችን …………….፣ዛፎችን……… በጣም አደገኛ ነው፡፡
3. ውሀን ማባከን ተፈጥሮን ያዛባል ዛፎችን መቁረጥ …………..
4. ተፈጥሮን መንከባከብ በሚለው መዝሙር ውስጥ ስንት ሩብ ኖታ እናገናለን…………..
5. የስነ ምግባር በሚለው በሚለው መዝሙር ውስጥ ስንት ግማሽ ኖታ አለ…………
6. ትምህርት ይጣፍጣል ከማር ከወተት ከማር ከወተት………..
7. ትምህርት ይጣፍጣል ከሚለው መዝሙር ውስት ስንት የሩብ ኖታ እረፍት ምልክት አለ………….
8. ውቢቷ ሀገራችን ለምለም እናታችን ትመግበናለች …………….

መልስ

1. እንከባከባቸው
2. መቅጠፍ፣መበከል እና መቁረጥ
3. መሬት ይሸረሽራል
4. 9
5. 3
6. ያርማል ስህተት
7. 3
8. እንደ ማር ወተት

፪ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ፃፉ::

1. ለ
2. ለ
3. ሐ
4. መ
5. መ

ዋቢ መፃህፍት


1. ታሪክና ምሳሌ፣ ክቡር ደ/ር ከበደ ሚካኤል (1999)
2. የኢትዮጵያ ታሪክ 1847-1983)፣ ባህሩ ዘውዴ
3. Ezra Abate, (2009) Ethiopian kinit (scales), Analysis of the formation and structure of the Ethiopian scale system
4. Ashenafi kebede ,( 1971) The music of Ethiopia ;its development and cultural setting
5. Ellinger, J. (2014) Music theory fundamentals
6. Jones, Russel and Cathrine ( 2021) , understanding basic music theory
7. Bahru Zwede ,(2002) The history of modern Ethiopia 1855- 1991
8. የኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ 1889-1983 ተስፋዬ ለማ (2005)
9. The little book of music theory, Amsco Publications, New York.
10. Harmony 1, Barrie Nettles, Berklee collage of music, (1987)

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# የ4ኛ ክፍል የክወናና የዕይታ ጥበባት መርሃ ትምህርት
## (Performing and Visual Arts Syllubus for Grade4)

ግንቦት 2013
ቢሾፍቱ

| የአራተኛ ክፍል የክወናና የዕይታ ጥበባት መርሃ ትምህርት |
| --- |
| ከዚህ ክፍል ትምህርት በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት<br>ከዚህ የክፍል ደረጃ በኋላ ተማሪዎች የሚከተሉትን ይችላሉ፡-<br>▪ የቅርፅ ዓይነቶችን፣ ፎርሞችን ልዩ ልዩ ቀለማትን ያስረዳሉ::<br>▪ የሙዚቃ ኖታዎች ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ከነእረፍት ኖታቸው ይለያሉ::<br>▪ የድምፅ አልባ ድራማ ይሰራሉ::<br>▪ መዝሙራትን ይዘምራሉ::<br>▪ ውዝዋዜዎችን ይወዛወዛሉ::<br>▪ ቁምና ዝርግ ፎቶግራፎችን ያስረዳሉ::<br>▪ በድምፅና በምስል የሚያዩዋቸውንና የሚሰሟቸውን መልክዕክቶችን ምስሎችንና ድርጊቶችን ያሳያሉ::<br>▪ የክሌፍ ዓይነቶችንና ክሌፎቹ የተቀመጡበትን ስታፍ መስመሮችና ባዶ ቦታዎች ከነረዳት መስመሮቻቸው ይለያሉ::<br>▪ በስታፍ ላይ (በስብስብ ላይ) የተፃፉትን (በመስመሮች ላይና በባዶ ቦታዎች ላይ የተፃፉትን) ሙዚቃዎች ይረዳሉ::<br>▪ ቤተሰባዊ ድርጊቶችን በመዝሙርና በውዝዋዜ ያከናውሉ::<br>▪ በተሰጣቸው ትዕዛዝ (መመሪያ) መሰረት ሥዕሎችን ሥለው፣ ኮላዥ ሰረተው፣ የሚቀባውን ቀብተው ያሳያሉ::<br>▪ የአገር በቀል ልምምዶች የሆኑትን የቤት አሰራሮችን፣ ማስዋቢያዎችን (ጌጣጌጦችን)፣ ሙዚቃዎችንና ጫወታዎችን ያደንቃሉ::<br>▪ በድምፅ አልባ ድራማና በመነባነብ መካከል ያሉትን ልዩነት ይለያሉ::<br>▪ በስዕልና በፎቶግራፍ መካከል ያሉትን ልዩነት ይለያሉ::<br>▪ ክ.እ.ጥ. ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን ጥመርታ ያስረዳሉ::<br>▪ የመዝሙራትን፣ የቅርፆችንና የቀለማትን አስፈላጊነት ያስረዳሉ::<br>▪ ውዝዋዜዎችን ከዕፅዋትና ከእንስሳት እንቅስቃሴዎች ይኮርጃሉ:: |

## የአራተኛ ክፍል የክወናና የዕይታ ጥበባት መርሃ ትምህርት

| የጭብጥ መስክ | ይዘት | የመማር ስልቶች | መማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|---|
| ጥበባዊ ግንዛቤ<br>( 25 ክፍለ ጊዜ) | ክፍል 1:<br>1. ማጤን -<br>1.1. ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ የተሰሩ መዝሙራትና ውዝዋዜዎች<br>1.2. የልዩ ልዩ ቅርፆች፣ ፎርሞችና ቀለሞች ጥናት<br>1.3. ድምፅ አልባ እንቅስቃሴን መረዳት<br>1.4. ዝርግና ቋም ፎቶግራፍ | • ተማሪዎች ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ድረስ የተዘጋጁ መዝሙራትን እንዲዘምሩ ይደረጋል፡፡<br>• በተሰጣቸው የድምፅና ቪዲዮ መሰረት መልዕቶችን፣ ምስሎችንና ድርጊቶችን እንዲለዩ ይደረጋል፡፡ | • የመለማመጃ ክፍሎች፣<br>• ምስሎች<br>• የሙዚቃና የቪዲዮ ማጫወቻ<br>• የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች | • ምልከታ<br>• የግል ጽብረቃ<br>• የቡድን ጽብረቃ |
| ፈጠራን መግለፅ<br>( 35 ክፍለ ጊዜ ) | ክፍል 2:<br>2. የግል/ የቡድን ክዋኔ<br>2.1. ስታፍና ክሌፎች<br>2.2. ባህላዊ ውዝዋዜዎች<br>2.2. ኮላዥን በአካባቢው ከሚገኝ ግብዓት ተጠቅሞ ፎርሞችን፣ ልስላሴና ሻካራነትን መስራት<br>2.4. መሠረታዊ ቀለማትና ቀጥተኛ ኅትመት<br>2.5. ፎርሞችና ልስላሴና ሻካራነት<br>2.4. የድምፅ አልባ ድራማና መነባነብ | • ስታፍ (ስብስብ) እንዲስሉና ስለመስመሮቹና ባዶ ቦታዎቹ እንዲያስረዱ ይደረጋል፡፡<br>• ክሌፎችን እንዲለዩና የስታፎቻቸውን መሠረታዊ የድምፅ መነሻ መስመሮችን እንዲለዩ ይደረጋል፡፡<br>• የመስመሮቹንና የባዶ ቦታዎቹን ከነረዳት መስመሮቻቸው ጭምር በሆሄ ስም እንዲለዩ ይደረጋል፡፡<br>• የቤተሰብን ድርጊቶች በሙዚቃና በውዝዋዜ እንዲያሳዩ ይደረጋል፡፡<br>በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ሥዕል እንዲስሉ፣ ኮላዥ እንዲሰሩና እንዲቀቡ ይደረጋል፡፡ | • የመለማመጃ ክፍሎች፣<br>• የሙዚቃና የቪዲዮ ማጫወቻ<br>• የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች<br>• የአካባቢ የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች ወዘተ.፣<br>• የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች<br>• እርሳስ፣ ጭቃ ከለርና በአካባቢው የሚገኙ ግብዓቶች | • ምልከታ<br>• የግል ጽብረቃ<br>• የቡድን ጽብረቃ<br>ግለማህደር |

## የአራተኛ ክፍል የክወናና የዕይታ ጥበባት መርሃ ትምህርት

| የጭብጥ መስክ | ይዘት | የመማር ስልቶች | መማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| **ታሪካዊና ባህላዊ አውዶች**<br><br>( 17 ክፍለ ጊዜ) | ክፍል 3:<br>3. ጥበብ በማኅበረሰብ ውስጥ ያለውጠቀሜታ<br>3.1. የክወናና የዕይታ ጥበባት በማህበረሰብ ውስጥ ከባህልና ከታሪክ አንፃር ያለው ሚና | • ታሪካዊ ቦታዎችን እንዲጎበኙ ይደረጋል፡፡<br>• የአካባቢውን ጥበባት<br>• በመዝሙራት<br>• በድምፅ አልባ ድራማና በመነባነብ<br>• በውዝዋዜ<br>እንዲከውኑ ይደረጋል፡፡<br>• የታወቁ ባህላዊ መዝሙራትን እንዲያጠኑ ይደረጋል፡፡<br>• የታወቁ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን እንዲያጠኑ ይደረጋል፡፡<br>• ቅርፆች እንዲለዩ ይደረጋል፡፡ የቤተሰባቸውንና የጓደኞቻቸውን የልብስ ቀለማት እንዲለዩ ይደረጋል፡፡<br>• የአካባቢያቸውን ባንዲራ ቀለማት እንዲለዩ ይደረጋል፡፡ | • የመለማመጃ ክፍሎች፣<br>• የሙዚቃና የቪዲዮ ማጫወቻ፤<br>• የአካባቢ የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች ወዘተ.፤<br>• ምስሎች<br>• የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች<br>• እርሳስ፣ ጭቃ ከሰርና በከባቢው የሚገኙ ግብዓቶች | • ምልከታ<br>• የግል ጽብረቃ<br>• የቡድን ጽብረቃ<br>• ግለማህደር<br>የቃል ጥያቄ |
| **ሥነ-ውበታዊ እሴት (ዋጋ)**<br><br>( 30 ክፍለ ጊዜ) | ክፍል 4<br>4. አድናቂነት<br>4.1. የክወናንና የዕይታን ጥበባት መለማመድ ያለው ጠቀሜታ (ዋጋ)፤<br>4.2. አገር በቀል የቤት አሰራሮችን፣ ጌጣጌጦችን፣ ሙዚቃዎችን፣ ጨዋታዎችንና | ተማሪዎቹ<br>• በዝማሬ፣<br>• በውዝዋዜ፣<br>• በድምፅ አልባ እንቅስቃሴና በመነባነብ፣<br>• ስዕል በመሳልና<br>• በፎቶግራፍ ስራ እንዲሳተፉና እንዲለማመዱ | • የመለማመጃ ክፍሎች፣<br>• የሙዚቃና የቪዲዮ ማጫወቻ፤<br>• የአካባቢ የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች ወዘተ.፤<br>• ምስሎች<br>• የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች፤ | • ምልከታ<br>• የግል ጽብረቃ<br>• የቡድን ጽብረቃ<br>• ግለማህደር<br>የቃል ጥያቄ |

## የአራተኛ ክፍል የክወናና የዕይታ ጥበባት መርሃ ትምህርት

| የጭብጥ መስክ | ይዘት | የመማር ስልቶች | መማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|---|
| | ወዘተ. ማወቅና ማድነቅ | ይደረጋል፡፡ | • እርሳስ፣ ጭቃ ከለርና በከባቢው የሚገኙ ግብዓቶች | |
| ጥመርታ ዝምድናና፣ ትግበራ<br>( 21 ክፍለ ጊዜ) | **ክፍል 5**<br>**5 ክ.እ.ጥ.ን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ፡፡**<br>5.1. ቅርፃችን፣ ፎርሞችንና ቀለማትን ከሒሳብ የትምህርት ዓይነትና ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ<br>5.2. የግል ንፅህና ላይ የዕቃዎች ንፅህና ላይና የአካባቢ ንፅህና ላይ ያተኮሩ መዝሙራት<br>5.3. ከዕፅዋትና ከእንስሳት እንቅስቃሴዎች ውዝዋዜዎችን መቅዳት | • ተማሪዎች በቡድናዊ ዝማሬ ወስጥ ምቱን ተከትለው በመወዛወዝ የሚና ጨዋታ በመጫወት ተፈጥሮን ለመግለፅ እንዲችሉ ግብዣ ይደረግላቸዋል፡፡<br>• ቅርፃችን፣ ፎርሞችንና ቀለማትን ከሒሳብ ትምህርት ዓይነትና ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማዛመድ እንዲተገብሩ ይደረጋል፡፡<br>• ተማሪዎች ስለተፈጥሮ (ስለከዋክብት፣ ስለወንዝ፣ ስለአዕዋፋት ወዘተ.) እንዲዘምሩ ይደረጋል፡፡ | • የመለማመጃ ክፍሎች፣<br>• የሙዚቃና የቪዲዮ ማጫወቻ፤<br>• የአካባቢ የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች ወዘተ.፤<br>• ምስሎች፤<br>• የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች፤<br>• እርሳስ፣ ጭቃ ከለርና በአካባቢው የሚገኙ ግብዓቶች | • ምልከታ<br>• የግል ጽብረቃ<br>• የቡድን ጽብረቃ<br>• ግለማህደር<br>የቃል ጥያቄ |

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓ.ም / 2021 /